# የኬባ ዳኛ ፤ የነብሰ ገዳይ ቁስ ፤ የደንቆሮ መምህርና የኢትዮጵያ ህልውና

## ከአይምሮ ዳኛቸው

የሀገራችን ኢትዮጵያ ህልውና ከዓመት ፤ ዓመት፤ ከቀን ፤ ወደቀን ወለሉ መድረሻ ወደሌለው እንጦሮንጦስ እያሽቆለቆለ የመጣ ፤ መፍትሄ የሌለውና መፍትሄውንም ባለማወቅ ሳይሆን አውቆ ለህዝብ ስውር እንዲሆንና ከሳት ወደ አረመጥ እየተሸጋገርን የውድ ሀገራችንን ግባተ መሬቷን እያጣደፍንና እያቀላጠፍን ያለነው እኛው ለሀገራችን አሳቢና ተቆርቋሪ ነን ባዮች ፤ በተቃዋሚነት ተሰልፈናል የምንል እንጂ ፤ አሁን በስልጣን ላይ ያለው የጎጠኛው ስርአት ወያኔ ብቻ እንዳልሆነ መገንዘብ የተሳነን ፤ ሃቅንና እውነውታን ፤ ካለማየትና ካለመስማት ፤ አውቀን የደነቆርን ፤ በፈቃዳችን የታወርን መሆናችን ከኛ የተሰወር አይደለም ። በየድረ ገጹና በየስብሰባው የምናደርገው ዘጥ ዘጥ ሁሉ ከአበካ ባይነትና ከአድር ባይነት የመነጨ እንደሆነ ከምንም የተሰወረ አይደለም ። ወደድንም ጠላንም ለጣሊያን ፋሽስት ይሰሩ ከነበሩት ሹምባሾችና ሹልቅባሾች ባንዳ ጋሻ ጃግሬዎች የባሰን እንደሆንን በግልጽ ይታያል ፤ ብጹዕ አባታችን አቡነ ጴጥሮስ በመስቀላቸው ፋሽስትን አውግዘው አርበኞችን ባርከው ሲሰዉ በየደብሩ በራፍ ቆሞ ስለሞሶሎኒ ኃያልነትና የኛ እርሱን መዋጋት አገርን ለማዳን መሞከሩ እግዚአብሄርን መጣላት ነው እያለ ይለፍፍ ከነበረው አጋቦስ ቁስ አልተሻልንም ። ጴጥሮስ በዚህች ሰዓት ብትኖር ምን ትለን ነበር? ብለን እራሳችንን መጠየቅ ከነበረብን ጊዜው አልፏል ። አሁንም እራሳችንን መመርመር የግድ ነው ። ይህንን መንፈስ ያካዘለ ጩኸት የጣልያን ወረራን የታገሉትን አርበኞች ፤ ያንድነት መንፈስ ፤ የትግል ቅላጤ ፤ ያካዘለ ትግል የወያኔን ጸረ ኢትዮጵያዊነት እንቅስቃሴን ሊገታው ከቶ አይችልም ።

ይህንን በፈቃደኝነት መደንቆራችንንና መታወራችንን የተረዱ የሀገርና የወገን ተቆርቋሪ በመምሰል ማንም ሳይመርጣቸው እራሳቸውን በመሪነት ያስቀመጡ ሹማምንቶች ግን እንደማትነጥፍ የወተት ከብት ላሜ ቦራ አድርገውን የደነዘዘውን የህብረተሰብ ክፍል የሚያልቡበት ትልቅ የገቢ ምንጫቸው ስለሆነ በደሀው የኢትዮጵያ ህዝብ ስም እየማሉና እየተገዘቱ ኪሳቸውን የሚያደልቡበት በመሆኑ ቀን ተሌት ተግተው ይህንን ዳፍንት የያዘውን የህብረተሰብ ክፍል ይባስ አይኑን ሊያጠፉለት እንደ ጦር በሰላና እንደ እሳት በጋለ ምላሳቸው አይኑንና ጆሮውን ጓጉጠው ከጥቅም ውጪ እንዲሆን አድርገውት እውር ድንብሩን ሲወራጭ ማየቱ የሚያሳዝን የጊዜያችን ታላቅ ድራማ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በመጀመሪያ አሁን በተቃዋሚነት ተሰልፈን ወያኔን እየታገልን ነው የሚሉት ብዙዎቹ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ፤ በማወቅ ይሁን ባለማውቅ ፤ የወያኔን እኩይ አላማ እያራመዱ ለመሆናቸው እኔ ብነግራችሁ ስለማትቀበሉ ጊዜና ወቅት ሲነግራችሁ ትደርሱበታላችሁና ስለነሱ ማንነትና ምንነት ብዙም ባላወጋ ፤ ነገር ግን አንዳንድ ነጥቦችን ላወሳ እወዳለሁ ። እዚህ ላይ በሃቀኝነትና በሐገር ወዳድነት በታኑኝ የወያኔን አገዛዝ ቀን ተሌት በከተማና በገጠር እየተዋጉና እየተዋደቁ ያሉ ሀቀኛ የኢትዮጵያውያን ድርጅቶች እንዳሉም ማስረገጥ እወዳለሁ ።

እስቲ ማን ይሙት የቅንጅት መሪዎች የምርጫ 97 እንዳለቀ ወደ እስር ከተወረወሩ በኋላ ምን የሚያመረቃ ትግል ተካሂዷል? ብለን እራሳችንን ብንጠይቅ መልሱ "እንዲያ ዝም

ነው የሚሆነው" ። ለማስረጃ ያክል እነዚህ ግለሰቦች ወደ እስር እንደተጋዙ አንድ ጊዜ ብቻ ትልቅ ሰላማዊ ሰልፍ እንደተደረገ ትዝ ይለኛል ። ወዲያው ብዙም ሳይቆይ KIL የሚባል የብተና ቡድን ከወያኔ ቤተመንግስታና ከቃሊቲ ተቀናጅቶ በለንደን አድርጎ በተግባር እንዲያውል የማፈራረሱ መሰረት ተጣለ ። ባይገርማችሁ አቃጁም ሆነ ተግባሪው ከወያኔ ጋር የተያያዘ መሆኑን እያወቅን ፤ ማወቅና መቀበል የማንፈልግ ወይም የማንቀበል ድፍኖች በመሆናችን አሁንም በድጋሚ ጊዜ ይንገራችሁ እንጂ እኔ የምለው አይኖረኝም ፤ ስለሁለቱም ብዙ ተብሎ ብዙ ተጽፏል ዛሬም የድርጅት ቁንጮ ስለሆኑ እንድትቀየሙኝና እንድታዝኑብኝ  አልፈልግም ። ብታምኑም ባታምኑም  ሀቁን ብናገርም ውሃ ከመውቀጥ በቀር የሚገኝ ትርፍ ስለሌለ አይናችሁንም ጆሮአችሁንም ሸብቦ የያዘው የደብተራን ትብትብ የሚያረክስ ምናምን  ይካክላችሁ ከማለት በቀር ብዙም የምለው አይኖረኝም ።

የነዚህ የዘመናችን ታላቅ ጉዶች ተግባር በዚህ ላይ ብቻ አላበቃም የተሰነጠቀ ቀዳዳ ከተገኘ በኋላ ከናካቴው ለማፈራረስ የሚያስችል AFD የሚባል የጉግ ማንጉግ ጥርቅም አሰባስበው የኢትዮጵያ አለኝታ ነውና ተቀበሉት በማለት በተለመደው የሰላ ምላሳቸውና የሚዲያ አሽቃባጮቻቸው ጋር በሞሆን እንደጠገበች አህያ ሲያናፋብን እንደከረሙ የምናስታውሰው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው ።

ወደር የለሹ የደናቁርት መንጋ የሆኑትን ተከታዮቻቸውንም ኧረ ቀስ በሉ ፤ እየተስተዋለ ፤ ብለን ብንመክር በምድር ላይ ያለም ፤ የሌለም  የስድብና የእርግማን ውርጂብኝ ወረደብን ። እንዴት ነው OLF እና ONLF ብሎ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ሊመጣ የሚችለው ብሎ የጠየቀ ሁሉ ውጉዝ ከማሪዮስ ተባሉ ። እውነትም ኢትዮጵያ አምላኳ ይጠብቃታል የሚባለው እውን ነው መሰለኝ ውሎም ሳያድር የውሀ ሽታ ሆነው ቀሩ ። አሁንም በጸረ KIL እና በጸረ AFD የቆምነው ላይ ጥርስ እንደተነከሰብን የምንናገረውና የምንሰነዝረው ሀሳብ ሁሉ ተቀባይነት አጥቶ ይባስ ብሎም በአፍራሽና በበታኝነት ሊፈርጁን ሲዳዳቸው ስመለከት ዘወትር አምላኬን የምለምነው እነዚህን የደናቁርት መንጋን "የሚሰሩትን አያውቁምና እባክህ ይቅር በላቸው"  ከማለት በቀር የምለው የለኝም ። በእብዶች  መንደር አንድ ጤነኛ ከእብድ ይቆጠራል እንደሚባለው ካበደው ጋር አብጄ የእብድ ተግባር ስተገብር አልገኝምና እርማችሁን አውጡ ።

እንዲያው እንዴት በወያኔ ልኡካን ትግሉ መላ ቅጡ ይጥፋ ብዬ እንጂ ካውራማ ካልኩ አመት ሙሉ ማውራት እችል ነበር ፡ እንዲያው ለምናልባቱ ጭራሹን ያልጠፋ የሞጨሞጨ ሊድን የሚችል  አይን ይኖር እንደሁ በማለት ነው የምዳክረው እንጂ ከተሰፈኛው ይልቅ ተሰፋ የቆረጠው እንደሚበዛ አላጣሁትም ።

በቅርቡም ከቃሊቲ እስር ተለቀቁ የተባሉት ጉዶች ወደ ምዕራቡ ዓለም መጡና ፈራርሶ የነበረውን ቤት ጭራሽ ሰደድ እሳት ለቀውበት እንደማይሆን እንዳደረጉት ለማንም የተሰወረ አይደለም ፡ በዚያም አላበቁም አሁንም የኢትዮጵያ አምላክ ነው መሰለኝ እነሱም ውለው ሳያድሩ ዘጠኝ ትንንሽ ሆነው አንዱ የብዕር ፤ ጦረኛ አንዱ የወያኔ ሙሽራ ፤ በመሆን ሰርጉንም ሳንበላ "ካንፋታ ተጋባን" ባሉን ማግስት ሳይጋቡ ተፋቱ የሚል ዜና ሰማን ።

አሁንም በወደቀ ዛፍ ላይ ምሳር የምታበዛ ተብዬ እንደምወቀስ ባላጣውም ፤ ነገር ግን ሳይወድቁም ጸረ ወያኔ ቡድኖች ሳይሆኑ ጸረ ወያኔ የሆነውን ቡድን ለመምታት በወያኔ ሰራሽነት የተቋቋሙ የቀን ለቀን ማጅራት መቺዎች እንደሆኑ ድሮም ያልኩት ስለሆነ የሚመጣብኝን ውርጂብኝ ከመጤፍም አልቆጥረውምና በከንቱ አትልፉ ።

ይልቁንም ለምን? እንዴት? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ከሃጢያት በመቁጠር እራሳችሁን አስራችሁ ተብትባችሁ ለዘረኛው ወያኔ ከማስረከባችሁ በፊት ፤ ምናልባት ወያኔ የራሱን ምስል በመወንጀልና በመኮነን የሌላ ወያኔያዊ አርበኛ ሊፈጥርልን ይሆን ብሎ መጠየቁም

አይከፋም ። ጥያቄ ማንሳትና ምናልባት ብሎ የጠላትን ስውር ደባ ለማወቅ መመርመር ወንጀልም ሃጢያትም አይደለምና ደም ስራችሁ ባይግተረተርና እራሳችሁን ከበሽታ ባትዳርጉት ይመረጣል ።

ማንም ይሁን ማን ከወያኔ ጋር ባለው የፖለቲካ ልዩነት ብቻ የታሰረን እደግፋለሁ ፤ ለሱም አርነት እታገላለሁ ፤ ያም ማለት ግን ጥያቄን ማንሳት አይከለክለኝም ፡ እንኳን ከልብ ነው ብዬ ባልቀበላቸውም ከወያኔ ጋር ግብ ግብ የያዙትን የተገንጣይ ቡድኖችንም ፍታ እያልን ካንቃችን እስኪላቀቅ እንቀድስ የለ ፡ የኢሕአፓ እስረኞች እስካልሆኑ ድረስ ።

ታዲያ እኛ እከሌ ማነው ፤ ከየት መጣ፤ ምንስ ይሰራ ነበር፤ ከነማንስ ጋር የተወዳጀ ነው፤ ብለን በጠየቅን የማርያም ጠላት ሆነን በነጋ በጠባ ይሄ ወያኔ በቀዶ ጥገና የተረተረውን አፋቸውን ሲያሟሹብን ይውላሉ ። ለዚህ ነው ትግሉ ከወያኔ ጋር መሆኑ ቀርቶ ወያኔን ያጠቃና ወያኔ ወያኔ የሚሸተውን ያጋለጠን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን እንደገባች ውሻ ሲሳደድ ቀን መሽቶ ቀን ይተካል ፡ ወያኔንማ ማን ነኪቶት ፡ ወያኔ ተንዘራፍቶና ተዝናንቶ እድሜ ለ 50 ሚሊዮን ዶላሬና ለ 52 ገጽ መመሪያዬ እንዲሁም ለታማኝ ሎሌዎቼ "አሳማውና ጉማሬው" እያለ ዛሬም በንጹሃን ደም እጁን እየታጠበ ያለፍርሀት ዋንጫውን እያጋጨ አራት ኪሎ ተወዝፎ ይገኛል።

"ለመሆኑ መስጠትን የማያውቅ ፤ አምጡን ማን አስተማረው"? የኛ ዘመነኞች ታግይ ተብዬዎች "እንቻቻል" "ህብረት" "አንድነት" እያሉ ሲያካዝኑ መስማት ለነ ጭፍኖ ይመስል ካልሆነ በቀር ለኔ "እንቻቻል" የሚለው አባካችሁ "ቻሉን" የሚል ያረጀ መዝሙር ሆኖ ነው የሚሰማኝ ፡ እስቲ አንተም ጀርባዬን እከክልኝ እኔም ጀርባህን ልክክልህ ብሎ መጠየቅ ያባት ሆኖ ሳለ የናንተን ተዉትና የኔን ብቻ ተቀበሉ ይሉናል ፤ ያውም የወያኔ ደቀመዝሙርነታቸውን እያወቅነው ። አይገርምም? ዘመነ ግርምቢጥ !

እነዚህ ተገንጣዩን OLF ን እና ONLF አቅፈው እሹሩሩ የሚሉ የአንድነትና የኢትዮጵያ ትንሳኤ አምጪዎች አድርጎ ከመቀበል ሳጥናኤል የየሱስ ደቀመዝሙር ነው ማለቱና ከዲያቢሎስ መስገዱ ይቀላል ። በአንፃሩ በትክክል ለኢትዮጵያ እየታገሉ ያሉትን እያወገዙና እየኮነኑ ሰው እንዲያይላቸው ቤተመቅደስ ገብተው እንባ እያፈሰሱ የሚማጸኑ ንጹሃን መስለው መታየትን የሚሹ ነገር ግን በጭለማ ተከናንበው ደግሞ ለባለዛርና ለቃሊቻ ሲሰግዱ የሚውሉ አስመሳዮች የአዞ እንባ የሚያነቡ የተካኑ የወያኔ ባለ ልዩ ማዕረግ ደቀመዛሙርት ናቸው ።

እነዚሁ ቡድኖች ናቸው ትላንት ሚኒሶታ ላይ "የምዬን ወዳብዬ" አድርገው የትግሬን ሕዝብ በቅንጅት ሥም ይቅርታ የጠይቁ "ማጥፋቱን ወታደር አጥፍቷል ፤ ግን ገበሬ ይካስ " ብለው አስደምመውናል ። ታዲያ ካቻምና ሲያጠፉ አልፈን ፤ አምና ሲያጠፉ አልፈን ፤ ዘንድሮም ሲያጠፉ አልፈን እንዴት ይቻላል ወይንስ ሁሌም ያጥፉ ልክ ናቸው ፤ ለወደፊትም ያጥፉ አታርሟቸው ነው ነገሩ? ውል አስይዙት እንጂ? እየተስተዋለ ጎበዝ !

ወያኔ ዘረኛ ፤ አፋኝ ፤ ጨካኝ ነው እያልን የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት ዛሬም እንደ ፈጣሪ ለምናመልካቸው ለነጮቹ አቤት እንበል እየተባለ ወጧ እንዳማረላት ሴት ሽር ጉዱ በየቦታው ተጧጡፏል ፡ እሺ ካላችሁ ይሁን እንግዲህ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ከሆነ ጥያቄው ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ እንጠይቅ ሲባል ፤ እንዴት ተደርጎ የኢሕአፓ እስረኞችንማ ከጠየቅን ጌታ ወያኔ ይቆጣሉና እሱ የማይሆን ነው ይሉናል ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ለኦጋዴና ለኦሮሞ ተገንጣዮች እናልቅስላቸው እያሉ ቂጣ በቀደደው አፋቸው ሳያፍሩ ይነግሩናል ። ታዲያ እነዚህ ናቸው በእውነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳቢና ለኢትዮጵያ ታጋዮች? እስቲ እራሳችሁን ጠይቁ ከወያኔ በበለጠ እኮ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት

የሚታገለውን ነው በቅድሚያ መታገልና መጣል የሚፈልጉት እንጂ የእንጀራ አባታቸውን ወያኔን እንዳልሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው ። "የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል" እንዲያው በለስ ቀንቷቸው የተመኙትን ቢያገኙ እኮ ቀድሞ ደርግ ሕዝቡን የደም እንባ ሲያስለቅስ ኃይሌ ማረኝ ተባለ ይላሉ ፤ አሁን ደግሞ ወያኔ ሕዝብ መግደል ብቻ ሳይሆን አገር እየገደለ ሲያዩ ፤ ደርግ በስንት ጣእሙ እያለ ነው ሕዝብ ይሉናል ፤ አሁን ደግሞ ወያኔ ሄዶ እነዚህ ወኔ ቢስ አሜኬላዎች ተተክለው ወያኔ የሚመሰገንበት ቀን ሊመጣ? አምላኬ ያንን ቀን ሳታሳየኝ ካሁኑ ወዳንተ መምጫ ቲኬት ቁረጥልኝ ብዬ መለመን ይሻለኛል እንጂ እዚያ ሰዓት ላይ ለመድረስ ምንም የምመኘው አይኖረኝም ።

ዛሬ ታዲያ  የሌባ ዳኛ ፤ የነብሰ ገዳይ ቄስ ፤ የደንቆሮ መምህር በላያችን ላይ ሾመን የኢትዮጵያን ትንሳኤ ልናመጣ ነው እያሉ መመፃደቅ ባያስቅም ማስገረሙ አልቀረምና ከምንሰራውና ከምናድርገው ነገር ሁሉ ቅን ልቦና ሰጥቶን መመርመርና ማዳመጥ ካልቻልን በዛሬው አያያዛችን መልስ እንደ ፊደል ካስትሮ 50ዓመት መግዛት ብቻ ሳይሆን እሱም ካለፈ በኋላ የሱ ልጅ ስልጣኑን ተረክቦ ዘወትር ሲያስለቅሰን እንደሚኖር ማመንና መቀበል የግድ ይሆናልና እራሳችንን እንመርምር ፤ የሰዎች ማንነት ሲጠየቅ ክብረነክ ነው እሳቸው በምን ሂሳብ ሊጠየቁ! እያሉ ግለሰቦችን ሰመያተ ሰማይ ማውጣትና መካብ ፤ ያልሆኑትን ሆኑ ፤ ናቸው ፤ በማለት በላያችን ላይ አንባገነን ማንገሱን እናብቃ ። "ተቀምጠው የሰቀሉት ቆመው ለማውረድ ይቸግራልና" ይታሰብበት ። መጠየቅና መጠርጠርም ሃጢያት እንዳልሆነ በምታምኑት መስኪድ ወይንም ቤተመቅደስ ሄዶ ማጣራቱ አይከፋም ። ትግላችን ግለሰቦችንም ቢያካትትም ዋናው ትግላችን ግን ለሐገርና ለአጠቃላይ ሕዝቧ ጭምር እንደሆነ አንዘንጋ ።

ማንኛውም ግለሰብ ሆነ ድርጅት አሁን አገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ በመጠየቁ ሊወቀስ ሊነቀስ አይገባውም ፤ ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ በመቃወሙ ሊታሰር ፤ ሊገረፍ ፤ ሊገደል ፈጽሞ አይገባም ፤ ይህ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ አቋም ሊሆን ይገባል ። የሚታሰሩ ግለሰቦች ወይም የድርጅት አባሎች እኔ ከማምንበት የፖለቲካ አቋም የተለየ ሊሆን ይችላል ። እንዲያውም እነዚህ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ስልጣን ላይ ቢወጡ ከወያኔ የተሻለ አቋምና አመለካከት ላይኖራቸው ይችላል ብዬ ላምን እችላለሁ ፤ ነገር ግን ከዚህ የፖለቲካ  እምነት  ተነስቼ ከኔ የተለየ አቋም ስላላቸው ብቻ ይታሰሩ ፤ ይገረፉ ፤ ይገደሉ ማለት የዲሞክሲ ፖለቲካን አለማወቅ ብቻ ሳይሆን ፤ የሰባዊነትና የሞራል ዝቅጠት ጭምር ነው ። ስለሆነም የነብርቱካን ሚደቅሳ እና መሰሎቿ መታሰርና መንገላታት ፈጽሞ የምንቀበለው ሊሆን አይችልም ። ብርቱካን ሚደቅሳ ሆነ ድርጅቷ ከኔ የፖለቲካ እምነት ጋራ የሚጣጣም አይደለም ፤ ነገር ግን በፖለቲካ እምነቷ የተነሳ መታሰሯን እሰየው የሚል የዲሞክራሲን ሀሁን የማያውቅ ነውና ሊወገዝ ይገባል ።

በአንጻሩ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችን በእምነታቸው የተነሳ ሲንገላቱ ፤ ለምሳሌ የኢሕአፓ የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ በሚነሳበት ወቅት አይመለከተንም ማለት ፤ ወይንም ጆሮ ዳባ ብሎ ማለፍ ፤ ምን ጊዜም ቢሆን ልንቀበለውና ቸል ብለን ልናልፈው የሚገባ ጉዳይ አይደለም ። እንዲያውም አዳዲስ የእስር ቤትና የግድያ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ በሄዱ ቁጥር እነዚህ ከማንኛውም እስረኛ የበለጠ ለረጅም ጊዜ ታስረውና ታፍነው ፤ ያሉበት ቦታና ሁኔታ በማይታወቅበት ወቅት ፤ የነሱን ሁኔታ ማንሳትና መጠየቅ የጊዜው የውይይታችንም ቀዳሚ አርእስት ማድረግና ለምናደርገውም ሰላማዊ ሰልፍና አለም አቀፋዊ ተቃውሞ ቅስቀሳ የተቀዳሚነት ስፍራ ሊሰጠው ይገባል ። ይህ ሳይሆን እያሌ ጊዜያቶች አልፈዋል ፤ ካሁን በኋላ ግንጥል ተቃውሞ መደረግ አይኖርበትም ። የምንደግፋቸውን ብቻ ስም ይዞ መሰለፍ ራሱ ልንቃወመው የሚገባ ጸረ ዲሞክራሲያዊና ጸረ ሰብአዊ እንቅስቃሴ ስለሆነ በቅድሚያ ልንዋጋውና እራሳችንንም ከዚያ ልናገል ይጠበቅብናል ። በመሆኑም ካሁን በኋላ የሚጠሩ ማናቸውም ሰላማዊ ሰልፎችና እንቅስቃሴዎች የኢሕአፓን እስረኞች የማያካትትና የማያነሳ ፤ ብሎም የማያስተዋውቅ ከሆነ ፤ የተለየ የተቃውሞና የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ የከሌ ከከሌ

ብሎ ሳይለይ ሁሉንም  የፖለቲካ እስረኞችን የሚያነሳ ሰላማዊ ሰልፍ በግለሰቦችም ይሁን በድርጅቶች መጠራት ይኖርበታል ። ዝምታው እስከመቼ ድረስ! ይሉኝታውስ ለምን? ማን እንዳያዝን? ልዩነቱም ሆነ አንድነቱም ከዚህ ይጀምራል ።  ይህ እስካልተፈጸመ ድረስ ትግሉ ቡድናዊ እንጂ ጠቅላላ ሰባዊነትን ያካተተ ስለማይሆን ልንታገልከው ይገባል ። አለያማ ትግሉስ ምኑን ትግል ሆነ!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!